## የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ምንነትና የመንግስት ግዴታዎች

ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ የሰብአዊ መብት ባለቤት ናቸው:: በመርህ ደረጃ ማንኛውም ሰው የመብቱ ተጠቃሚ ነው ማለት ነው:: ነገር ግን በተግባር አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ከሌሎቹ ባነሰ መልኩ የመብታቸው ተጠቃሚ ሲሆኑ ይታያሉ:: ይህም ሊሆን የቻለው በታሪክ ሲፈፀምባቸው በነበረው አድሎአዊነት ለጥቃት የተጋለጠ (Vulnerable) ሁኔታ ላይ በመሆናቸው ነው:: ይህ ሁኔታ ህፃናት፣ ሴቶች፣ ድሆች፣ አረጋውያን፣ ጉዳተኞችንና (የአካልና የአእምሮ) የመሳሰሉትን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህላዊ መብቶቻቸውንና የሲቪልና የፖለቲካ መብቶቻቸውን ለመቀዳጀት እንዳይችሉ አድርገዋል:: በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሌሎች እኩል የመሠረታዊ መብቶቻቸውና ነፃነታቸውን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ የህግ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል::

የሰቪልና የፖለቲካ መብቶች የአመለካከትን እና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ ፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት፣ ለፖለቲካም ሆነ ለሌላ አላማ የመደራጀት፣ ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብትና የመሳሰሉትን የሚያካትቱ ናቸው:: የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ መብቶች ደግሞ ተገቢ የሆነ የኑሮ ደረጃ የመምራት መብት፣ ለቤተሰቦች ድጋፍ የማግኘት መብት፣ የመስራትና የማኅበራዊ ደህንነነት መብት፣ የንብረት መብት፣ በኅብረተሰቡ የባህል ህይወት ውስጥ የመሳተፍና የመሳሰሉት መብቶች ናቸው::

ስለሆነም የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች የማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ አለመረጋጋቶች በሰው ልጆች ክብር፣ ነፃነትና አኩልነት ላይ የሚያስከትሉትን አደጋ ለመከላከል የተደነገጉ አለም አቀፍ እውቅና የተሰጣቸው መብቶች ናቸው::

የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች በኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕላዊ መብቶች አለም አቀፍ ቃልኪዳን እና በሰብአዊ መብቶች አለም አቀፍ መግለጫ እንደተዘረዘሩት፣

- ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት፣
- በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሠማራትና ለመተዳደሪያ የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት፣
- የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት፣
- የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ሥራ አጦችና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህፃናት ሕይወታቸውን በክብር እንዲመሩ እንክብካቤ የማግኘት መብት፣
- ለቤተሰቦች የእገዛና የጥበቃ መብት፣
- በቂ የሆነ ኑሮ ለመኖር የሚያስችሉ እንደ ልብስ፣ መጠለያና ምግብ የማግኘት መብት
- የንብረት መብት
- የጤና አገልግሎት የማግኘት መብት
- አጥጋቢ የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እድል የማግኘት መብት፣
- በህብረተሰቡ የባህል ሕይወት ውስጥ የመሳተፍ መብት እና ሌሎችን ያጠቃልላሉ::

የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብት መከበር ማለት ማንኛውም ሰው ክብር የተላበሰ ደህንነቱ የተረጋገጠ የማኅበራ ዊ ህይወት የመምራት መብት አለው ማለት ነው:: ወይንም ማንኛውም ሰው ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢና ደህንነቱንና እምቅ ችሎታውን የሚተገብርበትን ሁኔታዎች የማግኘት መብት አለው::

በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙት የኢኮኖሚክ፣ ማኅበራ ዊና ባህላዊ መብቶች ዜጐች ሊጠይቋቸውና ተጠቃሚ ሊሆኑባቸው የሚችሉት መንግስታት የአለማቀፉን ቃልኪዳን በመፈረምና በማጽደቅ እራሳቸውን ሲያስገድዱ ነው::

በኢትዮጵያ የአለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ የባህላዊና የባህል መብቶች አለም አቀፍ ቃል ኪዳንን ስምምነት አጽድቃለች:: በቃልኪዳኑ የተደነገጉትን መብቶች እንዲፈፀሙ መንግስትን የሚያስገድዱ ተመሳሳይ ድንጋጌዎች በኢፌዲሪ ህገ መንግስት ውስጥ ተካተዋል:: በዚህ በቃል ኪዳን ስምምነቱ መሠረት የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶችን ለመተግበር ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደ ደረጃ ተገቢውን እርምጃ እንድትወስድ ያዛል::

በመሆኑም እነዚህን መብቶች በተግባር ለማዋል የኢትዮጵያ መንግሥት የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ አለበት:: የመጀመሪያው ግዴታ የማክበር ግዴታ መንግስት እነዚህን የዜጐቹን መብቶች እንዳይጥስ ያስገድደዋል:: መንግስት የግለሰብ፣ የንብረት መብት፣ ግለሰቡ የመረጠውን ሥራ የመፈለግ መብቶችና ንብረቱን በግሉ ወይም ከሌሎች ጋር ለሚፈልገው አላማ የማዋል ነፃነቱን ማክበር አለበት:: በመሆኑም የአነስተኛ ቦታ ባለይዞታዋችንና indegenous ሰዎች የይዞታ መብትን እውቅና የመስጠትና መመዝገብ የማክበር ግዴታው ክፍል ነው:: ይህን በማድረግም መንግስት ባለይዞታዎቹ በተሻለ ደህንነት የሀብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑና በቂ የሆነ ህይወት? ለመኖር በሚያደርጉት ጥረት ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል:: በተጨማሪም መንግስት የዜጐችን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶችን የሚጥሱ ወይም የሚያጣብቡ ህግጋትን ማወጅ እንደሌለበት ይደነግጋል::

የማስከበር ግዴታ ደግሞ መንግስት ሶስተኛ ወገኖች የሚያደርሱትን የመብት መተላለፍ ለመከላከል ወይም የተላለፉት ላይ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ሕጐችን እንዲያወጣና ይህንኑ እንዲያስፈጽም ይገደዳል:: በዚህ ረገድ የመንግስት ግዴታ የሰዎች መብትን የሚተላለፉ ግለሰቦች በአፋጣኝ ለፍርድ ቀርበው ተገቢውን ቅጣት ለመስጠትና በደል የተፈፀመባቸው ካሳ ሊያገኙ የሚያስችሉ ህግጋትን ማውጣትና ጠንካራና ብቃት ያላቸውን ተቋማት ማቋቋምን ያጠቃልላል::

የመንግስት የማሟላት ግዴታ መንግስት ቅድሚያ መስጠት የሚገባውን ጉዳይ በድጋሚ እንዲያይና ተገቢውን የህግ፣ የአ- ስተዳደር፣ የበጀት፣ የዳኝነትና ሌሎች እነዚህን መብቶች በተግባር ለማዋል የሚያስችሉ ለውጦችን ማድረግ ያጠቃልላል:: በዚህ ረገድ መንግስት የማንኛውም ሰው የኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶችን መጠቀም መርዳትና ማሟላት አለበት:: ለምሳሌ በኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራ ዊና ባህላዊ መብት አንቀጽ 11(2) ቴክኒካዊና ሳይንሳዊ እውቀትን በመጠቀም የምግብ አመራረት፣ ክምችትና ስርጭት ዘዴን ለማሻሻል፣ የአልሚ ምግብ መረጃዎችን ለማሠራጨት፣ የተመጣጠነ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀም እንዲኖር የግብርና ሥርዓቱን ለማሻሻል አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች የመውሰድ ግዴታ አለበት:: የማሟላት ግዴታ መሠረታዊ ፍላጐቶችን ለማሟላት ሥራ አጥነት ሲከሰት፣ ለአረጋውያንና ለጉዳተኞች እንዲሁም ያልታሰበ ቀውስ ወይም እጦት ሲከሰትና ለተገለሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጥ ቀጥታ የምግብ ወይም የማኅበራዊ ደህንነት እርዳታን ማቅረብን ያካትታል::

አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ቃልኪዳን ስምምነት አንቀጽ 28 መሠረት ፌዴራላዊ አስተዳደር ያላቸው አገሮች የዚህ ቃልኪዳን ድንጋጌዎች በሁሉም የአስተዳደር ክፍሎች ያለምንም ገደብ ወይም ልዩነት ተፈፃሚ ይሆናሉ ስለሚል የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት በተመሳሳይ መፈፀም ይጠበቅባቸዋል::

የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች በሙሉ ሊከበሩ የሚችሉት በሂደት ነው:: ገንዘብና ጊዜ ሊያስፈልግ ይችላል::

የኢኮኖሚ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶችን ማስፈፀም ብዙውን ጊዜ ገንዘብ ስለሚጠይቅ እንደኢትዮጵያ ያሉ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ያለባቸውን ግዴታ በአንድ ጊዜ በበቂ ሁኔታ ሊወጡ አይችሉም፡፡ ነገር ግን ሁሉም የመንግስት ግዴታዎች መንግስትን ብዙ ገንዘብ የሚጠይቁ አይደሉም፡፡ አንዳንድ በቃል ኪዳን ስምምነቱ ላይ የሰፈሩ ግዴታዎችን ወዲያውኑ በተግባር ላይ ማዋል ይቻላል፣ ለመጥቀስ ያህል የማክበርና የማስከበር ግዴታዎችን ማንሳት ይቻላል፡፡

የአንድ ኅብረተሰብ ብሔራዊ ገቢ ብቻ ሳይሆን መንግስት የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት በማስከበር ረገድ ያለበትን ግዴታ ለመወጣት የሚመድበው የሃብት መጠንም መታየት አለበት፡፡ መንግስት የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶችን ለመተግበር በየአመቱ እየጨመረ የሚሄድ ሃብት መመደብ እንዳለበት በቃልኪዳን ስምምነቱ ግዴታ ተጥሏል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ መንግስት ከሌሎች አላማዎች አንፃር ለኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ማስከበሪያ የሚወስደው ምርጫም እንዲሁ መታየት የሚገባው ነው፡፡ በተለይ ለአገር መከላከያ እየተባለ የሚወጣው ሀብት በዚህ ረገድ ሊፈተሽ ይገባል፡፡

ለነዚህ መብቶች መተግበር ሙስና እንቅፋት እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ድሀ አገሮች ውስጥ ሙስና ከፍተኛ የሰብአዊ መብት መከበር እንቅፋት ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ገንዘብ የትምህርትና ሌሎች የማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ላይ ቢውል ለበርካታ ችግረኞች፣ ሴቶችና ህፃናት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች የማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ችግሮች ይፈቱ ነበር፡፡ ስለሆነም መንግስት የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና የባህል መብቶችን ለማስከበር ሙስናን መዋጋት ተቀዳሚ እርምጃው ሊሆን ይገባል፡፡

የማንኛውም ዜጋ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቱ መጠበቅ የመንግስት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት መሆኑን አውቀን የሰው ልጅ በእኩልነትና በክብር ሁሉም የሰብአዊ መብቶቹን ያለምንም አድሎና ልዩነት የሚጠቀምበትን ሥርአት ለመገንባት ለሚደረገው ጥረት ሁላችንም የበኩላችንን እናድርግ፡፡

★★★

*ይህን አጭር ጽሁፍ ያዘጋጀው አክሽን የባለሙያ ዎች ማህበር ለህዝብ (አፕአፕ) ነው፡፡ አፕአፕ በ1985 ዓ.ም የተቋቋመ አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን የተቋቋመበትም አላማ ህግና ሰብአዊ መብትን በመጠቀም የድሆችን በተለይ የሴቶችና የህጻናትን ሰብአዊ መብቶችን ማስከበር ነው፡፡*

*ለበለጠ መረጃ ከታች በተቀመጠው አድራሻ ያነጋግሩን፡፡*


ስድስት ኪሎ፣ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል
በሚወስደው መንገድ ፤
ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትን አለፍ ብሎ፣
አዲስ የተሰራው የቴሌኮሚዩኒኬሽን ህንፃ ፊት ለፊት
ፖ.ሣ.ቁ. 12484፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ 251-11-1-243555፣ፋክስ 251-11-1243558
ኢ-ሜይል፡apap@ethionet.et
ዌብ ሳይት(ድረ-ገፅ):
**http:**\\www.devinet.org\apap


# ሰብአዊ መብቶች

## ከስጋትና ከመሰረታዊ ፍላጎት እጥረት ነጻ ሆነው የመኖር መብት እንዳለዎት ያውቃሉ?

**አክሽን የባለሙያዎች ማህበር ለሕዝብ (አኘአኘ)**